# መሻር በዲሲ

A *ሕጋዊ ሽረት* ትዳር ተቀባይነት እንደሌለው የፍርድ ቤት ውሳኔ ነው። ህጋዊ ሽረት ትዳር ይሰርዛል - የዚህ ህጋዊ ውጤትም ትዳሩ እንዳልተካሄደ ነው። A *ሀይማኖታዊ ሽረት* ይህ ከህጋዊ ሽረት ይለያል። ስለ ሃይማኖታዊ ሽረት ማወቅ ከፈለጉ የሀይማኖት ባለሹመትዎን ይጠይቁ። ሕጋዊ ሽረት በተጨማሪም ከፍቺ ይለያል። ፍቺ ህጋዊ ጋብቻ ያፈርሳል።

**ትዳሬ እንዲሻር ማድረግ እችላለሁ?**

ዲሲ ውስጥ ሽረት በጣም ያልተለመደ ነው። ትዳር እሚሻረው በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ሲሆን፣ እነዚህም በብዛት አይፈጠርም። የዲሲ ህግ ትዳር እንዲሻር ፍርድ ቤት እንዲጠይቁ የሚችሉት በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፡

- ከትዳር አጋሮ ጋር ሲጋቡ ከሁለት አንዳቹህ ትዳሩን ለመቀበል በአእምሮ ችግር ምክንያት ካልቻሉ፡
- የትዳር አጋሮን ያገቡት ባደረሱቦት ጫና ወይ ማታለያ ከሆነ ፡
- የትዳር አጋርዎን ሲያገቡ ከ16 ዓመት በታች ከነበሩና 16 ዓመት ሲሞላዎት በትዳር ውስጥ እንደ ባልና ሚስት መኖር ፈቃደኛ ካልሆኑ ፡
- የትዳር አጋሮን ሲያገቡ ከሁለት አንዳቹ ሌላ ህጋዊ ትዳር ነበሮት፡
- የቅርብ ዘመድ ካገቡ።

ፍርድ ቤቱ አንድ ወይ ከዛ በላይ የተጠቀሱትን ቅድመሁኔታዎች እንዳሟሉ ካመነ ትዳሮን ሊሽር ይችላል።

**ትዳሬ እንዲሻር የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለብኝ?**

ህጋዊ (ሃይማኖታዊ ሳይሆን) ሽረት ከፈለጉ፣ በሚከተሉት ምክንያቶች ምክንያት እንዲሻር ከፈለጉ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ያስፈልጎታል፡

- ከትዳር አጋሮ ጋር ሲጋቡ ከሁለት አንዳቹህ ትዳሩን ለመቀበል በአእምሮ ችግር ምክንያት ካልቻሉ፡
- የትዳር አጋሮን ያገቡት ባደረሱቦት ጫና ወይ ማታለያ ከሆነ ፡
- የትዳር አጋርዎን ሲያገቡ ከ16 ዓመት በታች ከነበሩና 16 ዓመት ሲሞላዎት በትዳር ውስጥ እንደ ባልና ሚስት መኖር ፈቃደኛ ካልሆኑ ፡

እነዚህ *ውድቅ ሊደረጉ የሚችሉ* ጋብቻዎች ተብለው ይጠራሉ።

ነገር ግን አንዳንድ ጋብቻዎች ከመጀመርያ ቀን ጀምሮ በሕግ *ተቀባይነት* የላቸውም (ይህም፣ ሰዎቹ በህጋዊ መንገድ ተጋብተው ካልነበረ)። የዲሲ ህግ ለሚከተሉት የትዳር ዓይነቶች እውቅና አይሰጥም፡

- ከቅርብ ዘመድ ጋር የሚደረግ ጋብቻ ወይ
- የቀድሞ ጋብቻው በሞት ወይ በፍቺ ያልፈረሰ ሰው ጋር መጋባት (ማለትም ከሁለቱ አንዱ ሌላ ሰው አግብተዋል ማለት ነው)።

የተጠቀሱት ሁኔታዎች እርስዎን የሚመለከት ከሆነ ፍቺ ወይ ሽረት ማግኘት አይጠበቅቦትም ምክንያቱ ጋብቻዎ ሕጋዊ ስላልነበረ። ነገር ግን፣ ጋብቻዎ ተቀባይነት እንዳልነበረው ለማረጋገጥ እንዲሻር ማመልከት ይኖርቦታል።

**በማህበራዊ ህግ ካገባሁስ?**

በማህበራዊ ህግ ወይ በፕሮግራም ለተደረገ ጋብቻ ተመሳሳይ የሆነ የሽረት ቅድመሁኔታ አለው።

**ሽረት ለመጠየቅ ዲሲ ለኔ ትክክለኛውቦታነው?**

ዲሲ ወስጥ ካገቡ ወይ በአሁኑ ግዜ ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ዲሲ ወስጥ እንዲሻርሎት መጠየቅ ይችላሉ።

**ሽረት መጠየቅ የሚችለውማነው?**

ሽረቱ የተጠየቀውአንደኛውአካል ከእድሜበታች ሆኖ ካገቡና ተጋቢው/ዋ አሁንም ከዕድሜበታች ከሆኑ (18 ዓመት በታች)፣ ከእድሜበታች የሆነ ው/ነ ችውወላጅ ወይ አሳዳጊ ከሆኑ እንዲሻር መጠየቅ ይችላሉ። ጋብቻውእንዲሻር የሚጠየቀውአንደኛውአካል ወሳኔ ለመወሰን የአእምሮ ችግር እንዳለበት ከታወቀ ያንን ሰውየሚንከባከበውአካል እንዲሻር መጠየቅ ይችላል።

የአእምሮ ችግር የሌለበት ሰውወይምከእድሜበታች ከሆነ "በስህተት"ሽረት መጠየቅ አይችልም። ለምሳሌ፣ ራሱ ማጭበርበር የፈፀመሰውበፈፀመውማጭበርበር ይሻራል። ማጭበርበር የፈፀመውሰውጋብቻውን ማቋረጥ ከፈለገ እሷ ወይ እሱ ለፍቺ ማመልከት አለባቸው። የተጭበረበረውሰውብቻ ሽረት ይሰጠዋል።

**እንዲሻር እንዴት ማመልከት እችላለሁ?**

ስለ ጉዳዮ ለጠበቃ ማማከር ወይ እራስዎት ማመልከት ይችላሉ። አስፈላጊ የሆኑትን የፍርድ ቤት *የፅሁፍ ክስ* በ www.dcbar.org/pleadings ወይ ዲሲ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ከፍተኛውየ ቤተሰብ ፍርድ ቤት መቀበያ ማእከል (500 Indiana Avenue NW, room JM-540),ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m ከፍት ነው።

**የትዳር አጋሬ እንዲሻር ካመለከተና ነገር ግን እኔ ካልተቀበልኩትስ?**

ለፍርድ ቤቱ ያልተስማመበት ምክንያትና ፍርድ ቤቱ ይህን ሽረት እንዳይቀበል መጠየቅ ይችላሉ።

**ሽረት ሲፈቀድ ፍርድ ቤት የሚያነሳቸውጉዳዮች ምንድን ናቸው?**

የጋራ ንብረት ወይ ልጆች ካላቹ ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ እንዲያይ መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎና አጋርዎ በነዚህ ጉዳይ ስምምነት ላይ ከደረሱ ፍርድ ቤቱ የናንተን ስምምነት የሚያመላክት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ካልተስማሙ፣ የፍርድ ሂደት ተደርጎ ዳኛውወሳኔ ይሰጣል።

**አበል ማግኘት እችላለሁ?**

ሸረቱ እንዲጠናቀቅ እስኪጠብቁ ፍርድ ቤቱ ግዝያዊ አበል እንዲሰጦት ሊወስን ይችላል፤ ነገር ግን ሸረቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አበል ማግኘት አይችሉም። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ‹‹አበል በዲሲ›› እሚለውን ይመልከቱ።

**ሸረቱ የሚጠናቀቀው መቼ ነው?**

ከፍርድ ሂደት በኋላ ዳኛው ሸረቱን ከፈቀዱ የዚህ ትእዛዝ ቅጂ ይሰጦታል። ሸረቱ የሚጠናቀቀው ‹‹ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ ቀን›› 30 ቀናት በኋላ ሲሆን ይህም ከፍርድ ሂደቱ የተወሰኑ ቀናት በኋላ ሊሆን ይችላል። ማንኛውም አካል በነዚህ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅና እንዲሁም ፍርድ ቤቱ የሸረት ትእዛዙን (ይህም፣ የመጨረሻ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት እንዲቆይ) እንዲያቆየው መጠየቅ ይችላሉ። እንዲቆይ ከተፈቀደ፣ ይግባኝ ጥያቄው ከተፈታ በኋላ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል። እንዲቆይ ካልተፈቀደ፣ አሁን ምትእዛዙ ከ30 ቀናት በኋላ የሚፈፀም ነው። ሁለታችሁም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ላለመጠየቅ ከተስማማቹ፣ የጋራ የይግባኝ ጥያቄ አለማንሳት በማስገባት 30 ቀን ሳትጠብቁ ውሳኔው ወድያው ይጠናቀቃል።